# አንድነት ፓርቲ ድክመቶቹን አርሞ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትክክለኛ አማራጭ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. ተመስርቶና ነሐሴ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. ከምርጫ ቦርድ የህጋዊ እውቅና ሰርተፊኬት አግኝቶ በሰላማዊ መንገድ ሲንቀሳቀስ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ የመሰረቱትም ህጋዊ ስልጣን ያላቸው 327 የሚሆኑ የፓርቲው መስራች የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ናቸው፡፡ እነዚሁ የመስራች ጉባኤ አባላት በእለቱ በአካል በመገኘት የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በማፅደቅና አመራሩን በመምረጥ የፓርቲውን መመስረት እውን አድርገዋል፡፡

አንድነት ፓርቲ በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች አባላትን በማደራጀት፣ ጽ/ቤቶችን በመክፈትና ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ በአጭር ጊዜ ተስፋ ሰጭ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ይሁንና ብዙም ሳይቆይ የፓርቲው ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከህግ አግባብ ውጭ ታስረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አመራሩን የያዙት አባላት ኃላፊነታቸውን መወጣትና ፓርቲው የቀመላቸውን አላማዎች ማስቀጠል አልቻሉም፡፡ ይልቁንም ችግሮች መኖራቸውና መወያየት እንደሚገባ ቢነገራቸውም በራቸውን ለውይይት በመዝጋት ህዝብን እያሳዘኑ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ፓርቲው በገጠሙት ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች ህልውናው አደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡

እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 27.1. አንድ ሦስተኛው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ከጠየቁ ልዩና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት በተነሱት ችግሮች ላይ ለመነጋገርና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከ327ቱ የመስራች ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት 111 አባላት ጉባኤው እንዲጠራ መፈለጋቸውን በፊርማቸው አረጋግጠዋል፡፡

ስለዚህ ሚያዝያ 10 ቀን 2002 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ2:00 ሰዓት ጀምሮ ቀበና፣ በኮከበ-ፅባህ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ልዩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስለሚደረግ የመስራች ጉባኤው አባላት በሙሉ ተጠርተዋል፡፡ አዘጋጅ ኮሚቴውም የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎችን በማሟላት ጥሪውን በመገናኛ ብዙኃን፣ በስልክና በጥሪ ወረቀት እያስተላለፈ ይገኛል፡፡ አባላቱም አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያን ህዝብ የስላጣን ባለቤት የማድረግ አላማውን እንዲያሳካ በጉባኤው ላይ በመገኘት የፓርቲውን ህልውና እንዲታደጉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!

የአንድነት ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ
መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም.